# ትንቢት እና ነቢያት ሁለተኛ ሳምንት

## ነቢይ

### የነቢይነት ጥሪ አገልግሎቶች

1. **የ እግዚአብሔርን መልዕክት ወይም የፍርድ ቃል ለህዝቡ መናገር** (የእግዚአብሔር ድምጽ ነው::)
2. **ስለ ወደፊት ትንቢት መናገር**
3. **በመገለጥ ማወቅ (የተሰወረን ማወቅ/መግለጥ)**
   - የጠራው ፈሪሳዊም አይቶ፦ ይህስ ነቢይ ቢሆን፥ ይህች የምትዳስሰው ሴት ማን እንደ ሆነች እንዴትስ እንደ ነበረች ባወቀ ነበር፥ ኃጢአተኛ ናትና ብሎ በልቡ አሰበ። (ሉቃ 7፥39)
   - ኢየሱስም፦ ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ አላት።ሴቲቱ መልሳ፦ ባል የለኝም አለችው። ኢየሱስ፦ ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤አምስት ባሎች ነበሩሽና፥ አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ እውነት ተናገርሽ አላት።ሴቲቱ፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ። (ዮሐ 4:16-19)
   - የሶርያም ንጉሥ ከእስራኤል ጋር ይዋጋ ነበር፤ ከባሪያዎቹም ጋር ተማክሮ፦ በዚህ ተደብቀን እንሰፍራለን አለ።የእግዚአብሔርም ሰው፦ ሶርያውያን በዚያ ተደብቀዋልና በዚያ ስፍራ እንዳታልፍ ተጠንቀቅ ብሎ ወደ እስራኤል ንጉሥ ላከ።የእስራኤልም ንጉሥ የእግዚአብሔር ሰው ወደ ነገረው ስፍራ ሰደደ፤ አንድ ጊዜም ሳይሆን፥ ሁለት ጊዜም ሳይሆን በዚያ ራሱን አዳነ።የሶርያም ንጉሥ ልብ ስለዚህ እጅግ ታወከ፤ ባሪያዎቹንም ጠርቶ፦ ከእኛ ዘንድ ከእስራኤል ንጉሥ ጋር የተወዳጀ እንዳለ አትነግሩኝምን? አላቸው።ከባሪያዎቹም አንዱ፦ ጌታዬ ሆይ፥ እንዲህ እኮ አይደለም፤ ነገር ግን በእልፍኝህ ውስጥ ሆነህ የምትናገረውን በእስራኤል ዘንድ ያለ ነቢይ ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ይነግረዋል አለ። 2ነገ 6:8-12)
   - ሸፍነውም ፊቱን ይመቱት ነበርና፦ በጥፊ የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገር እያሉ ይጠይቁት ነበር። (ሉቃ 22፥64)

4. **ድንቆችንና ተአምራትን ማድረግ**
   - የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ ሊናገርም ጀመረ፥ ለእናቱም ሰጣት።ሁሉንም ፍርሃት ያዘቸውና፦ ታላቅ **ነቢይ** በእኛ መካከል ተነሥቶአል፥ ደግሞ፦ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጐበኘ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።(ሉቃ 7:16)
     *(ኢየሱስ የሞተውን ሲያስነሳ ነቢይ በመካከላችን ተነስቷል አሉ)*
   - አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ፥ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረካቸው ቆርሶም ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ።ሁሉም በልተው ጠገቡ፥ ከእነርሱም የተረፈውን ቍርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ወሰዱ። ...... እነርሱም መልሰው፦ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም፦ ኤልያስ፥ ሌሎችም፦ ከቀደሙት **ነቢያት** አንዱ ተነሥቶአል ይላሉ አሉት።
   - በመካከላቸውም መለያየት ሆነ። ከዚህም የተነሣ ዕውሩን፦ አንተ ዓይኖችህን ስለ ከፈተ ስለ እርሱ ምን ትላለህ? ደግሞ አሉት፦ እርሱም፦ **ነቢይ** ነው አለ።(ዮሐ 9:17)
5. **የምሪት የምክር ቃል መስጠት** :: በመለኮታዊ ምሪት መካሪ( የምሪት ቃል ሰጪ) ነው::
   - ኢዮሣፍጥም፦ በእርሱ **እግዚአብሔርን የምንጠይቅበት** የእግዚአብሔር ነቢይ በዚህ አይገኝምን? አለ። ከእስራኤልም ንጉሥ ባሪያዎች አንዱ፦ በኤልያስ እጅ ላይ ውኃ ያፈስስ የነበረው የሣፋጥ ልጅ ኤልሳዕ እዚህ አለ ብሎ መለሰ።(2 ነገ 3፥11)

ትንቢት የሚናገር ሁሉ ነቢይ አይደለም:: የትንቢት ጸጋ ያለው ነው እንጂ::

1. የአጠራሩ ባህርይ::
   - ከእግዚአብሔር ከኢየሱስ ክርስቶስ ልዩ ጥሪ

- በሌላ ነቢይ መቀባት (ኤልሳእ በኤልያስ)

2. የሥራው አይነትና ባህርይ
   - ወንድሞች ሆይ፥ የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ።(ያዕ 5:10)
   - ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወኅኒ ተፈተኑ፤በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፥ ተፈተኑ፥ በመጋዝ ተሰነጠቁ፥ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፥ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ። (ዕብ 11: 36-38)

# ክፍል አንድ
# አቀባበል

## 1. ነቢያትን እንዴት እንቀበል?

**ነቢያትን አቀባበል በሚመለከት ሦስት አይነት አቋም አለ**

1ኛ) የነቢያትን ቃል እንደ መጨረሻ የሥልጣን ቃል አድርገው እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚወስዱ አሉ::
2ኛ) ነቢያት የሉም ካሉም አያስፈልጉም: የሚሉ የሚንቁ የሚያጣጥሉ አሉ
3ኛ) እውነተኛ ነቢያት አሉ ሀሰተኛም ነቢያት አሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል መርምረን ልንቀበል ይገባል የሚሉ ናቸው::

*መርምረን እንቀበል*

### 1.I በክርስቶስ የነቢይነት ምሳሌነት ሥር እንቀበል ....

- በክርስቶስ ኢየሱስ የነቢይነት ምሳሌነት በመመርመር (በብሉይ ኪዳን ነቢያት ዋና ምሳሌነት ሳይሆን በአዲስ ኪዳን ነቢያት ምሳሌነት

### 1.II ክርስቶስ በሚመለከት ባላቸው ትምህርት- (Doctrine of Christ)....

- በነገረ ክርስቶስ አስተምህሮ በመመርመር (ስለ ክርስቶስ ባላቸው አስተምህሮ)

### 1.III በክርስቶስ ኢየሱስ የህይወት ምሳሌነት በመመርመር

- ህይወታቸው ክርስቶስ ኢየሱስን ይመስላል ወይ?—በህይወታቸው ፍሬ ...
- ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ- የመንፈስ ፍሬ በህይወታቸው ይታያል ወይ?

### IV. የሚያመጡት የትምቢት መልዕክት ይዘት

የትንቢት መልእክታቸውን ይዘት በመመርመር -ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ባለው መስማማት...

### 1.V. በጥሪያቸው እንቀበል

ነቢይን እንደ እንደ ነቢይ

- ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። (ማቴ 10፥41)

- ✓ (እውቅና መስጠት በግልም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ አስፈላጊ ነው :-ምደባን ወይም ሹመትን ወይም ለጌታ መለየትን መስጠትን ጨምሮ።)
- ✓ ቤተ ክርስቲያን የጥሪውን አገልግሎት የምትፈታው ለጥሪው እውቅና በመስጠት እና ለጌታ በመለየት ይፋ በማድረግ ነው።
- ✓ በቤተ ክርስቲያን የጥሪው አገልግሎት በሙሉ ሥልጣኑ ሥራ ላይ የሚውለው/የነቢይነትን ዋጋ የምትቀበለው ቤተ ክርስቲያን ለጥሪ አገልግሎቱ የሚገባውን ስፍራ እና ሥልጣን በአግባቡ በሰጠችው ልክ ነው። (ግዴታ አይደለም።)

- አንድ ቀንም እንዲህ ሆነ፤ ኤልሳዕ ወደ ሱነም አለፈ፥ በዚያም ታላቅ ሴት ነበረች፤ እንጀራ ይበላ ዘንድ የግድ አለችው፤ በዚያም ባለፈ ቍጥር እንጀራ ሊበላ ወደዚያ ይገባ ነበር። ለባልዋም፦ ይህ በእኛ ዘንድ ሁልጊዜ የሚያልፈው ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ሆነ አውቃለሁ። ትንሽ ቤት በሰገነቱ ላይ እንሥራ፤ በዚያም አልጋ ጠረጴዛ ወንበርና መቅረዝ እናኑርለት፤ ወደ እኛም ሲመጣ ወደዚያ ይገባል አለችው። አንድ ቀንም ወደዚያ በመጣ ጊዜ ወደ ቤቱ ገብቶ በዚያ ዐረፈ። … እርሱም: በሚመጣው ዓመት በዚህ ወራት ወንድ ልጅ ትታቀፊአለሽ አለ፤ (2ነገሥ 4: 9-11; 16)

## I.VI. እንደኛ ሰው እንደሆኑ በመገንዘብ

- ❖ እውነተኛ ነቢያት ሊስቱ: ሊሳሳቱ: ሊያያስቱም ይችላሉ። በምን ምክንያት ተሳሳቱ? ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅጣትን የሚያስከትል ሁሉ ሊሆን ይችላል። ሁሉም ስህተተ የሚያስቀጣ ባይሆንም:

**ኤልያስ**

- ኤልያስ እንደ **እኛ የሆነ ሰው ነበረ**፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥(ያዕ: 5፥17)
- ኤልዛቤልም፦ ነገ በዚህ ጊዜ ነፍስህን ከእነዚህ እንደ አንዲቱ ነፍስ ባላደርጋት፥ አማልክት ይህን ያድርጉብኝ ይህንም ይጨምሩብኝ ብላ ወደ ኤልያስ መልእክተኛ ላከች። ኤልያስም ፈርቶ ተነሣ፥ ነፍሱንም ሊያድን ሄደ፥ በይሁዳም ወዳለው ወደ ቤርሳቤህ መጥቶ ብላቴናውን በዚያ ተወ። እርሱም አንድ ቀን የሚያህል መንገድ በምድረ በዳ ሄደ፤ መጥቶም ከክትክታ ዛፍ በታች ተቀመጠና፦ ይበቃኛል አሁንም፥ አቤቱ፥ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ ብሎ እንዲሞት ለመነ። (1ነገሥ 19: 2-4)

**ሙሴ**

- እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ በትርህን ውሰድ፤ አንተና ወንድምህ አሮን ማኅበሩን ሰብስቡ፥ ድንጋዩም ውኃን እንዲሰጥ እነርሱ ሲያዩ ተናገሩት፤ ከድንጋዩም ውኃ ታወጣላቸዋለህ፤ እንዲሁም ማኅበሩን ከብቶቻቸውንም ታጠጣላቸዋለህ።ሙሴም እንደ ታዘዘ በትሩን ከእግዚአብሔር ፊት ወሰደ። ሙሴና አሮንም ጉባኤውን በድንጋዩ ፊት ሰብስበው፦ እናንተ ዓመፀኞች፥ እንግዲህ ስሙ፤ በውኑ ከዚህ ድንጋይ ውኃን እናወጣላችኋለን? አላቸው። ሙሴም እጁን ዘርግቶ ድንጋዩን ሁለት ጊዜ በበትሩ መታው፤ ብዙም ውኃ ወጣ፥ ማኅበሩም ከብቶቻቸውም ጠጡ።እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን፦ በእስራኤል ልጆች ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ በእኔ አላመናችሁምና ስለዚህ ወደ ሰጠኋቸው ምድር ይህን ጉባኤ ይዛችሁ አትገቡም አላቸው። (ዘኍ 20:10)

**ናታን**

- ንጉሡ ነቢዩን ናታንን፦ እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት ተቀምጬአለሁ፥ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በመጋረጆች ውስጥ እንደ ተቀመጠ እይ አለው። ናታንም ንጉሡን፦ እግዚአብሔ በዚያም ሌሊት የእግዚአብሔር ቃል ወደ ናታን መጣ እንዲህም አለው፦ር ከአንተ ጋር ነውና ሂድ፥ በልብህም ያለውን ሁሉ አድርግ አለው። ሂድ፥ ለባሪያዬ ለዳዊት ንገረው፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ምድር ካወጣሁበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በድንኳንና በማደሪያ እሄድ ነበር እንጂ በቤት አልተቀመጥሁምና አንተ የምኖርበትን ቤት አትሠራልኝም። (2 ሳሙ 7: 2.6)

**ሳሙኤል**

- እንዲህም ሆነ፤ በመጡ ጊዜ ወደ ኤልያብ ተመልክቶ፦ በእውነት እግዚአብሔር የሚቀባው በፊቱ ነው አለ። እግዚአብሔር ግን ሳሙኤልን፦ ፊቱን የቁመቱንም ዘለግታ አትይ፤ ሰው እንዲያይ እግዚአብሔር አያይምና ናቅሁት፤ ሰው ፊትን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል አለው። (1ሳሙ 16፥6-7)

# ትንቢትን እንዴት እንቀበል?

*ትንቢትን እንዴት እንቀበል?*

## *I. መርምረን እንቀበል*

A. በእግዚአብሔር ቃል ገዥነት እና ባለሥልጣንነት ሥር በመመርመር
   - ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን ትንቢት በሙሉ የሀሰት ትንቢት ነው::
     (ትዳርን የሚያፋታ ትንቢት ቤተ ክርስቲያንን የሚከፋፍል ቤተሰብን የሚለያይ ትንቢት ወዘተ...)

B. በጊዜ ሂደት ውስጥ በማየት እንቀበል
   - ለጊዜ ዳኝነት የሚተው ትንቢቶች አሉ

## *II. የትንቢቱን ባህርይ በመለየት እንደ ባህርይው እንቀበል*

### 1. የትንቢት ባህርያት

- የትንቢት አተረጓጎም ከትንቢት ባህርያት የሚመነጭ ነው:: ትንቢትን ለመተርጎም የትንቢቱን ባህርይ መረዳት ወሳኝ ነው::
- ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል። (ለማፍረስ አይደለም)

### *ሀ) የጸና የትንቢት ቃል / መጽሐፍ ቅዱስ*

ጌታ ኢየሱስ የነቢያት ሁሉ የበላይ እና ገዥ እንዲሁም ባለቤት እንደሆነ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የትንቢቶች ሁሉ ገዥ የትንቢት ቃል ነው:: ሁሉንም ትንቢቶች መመርመሪያ ገዥ ቃል ነው::

- ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፥ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ። (2ጴጥ 1፥19)

### *ለ) ቅድመ ሁኔታን አዘል*

1. ቅድመ ሁኔታ ያለው የትንቢት መልዕክት
   - በእምነት በጸሎት ኋላፊነት በመወጣት ፈቃዱን በመፈጸም ዲያብሎስን ጸንተን በመቃወም የምቀበለው እና ለተፈጻሚነቱ በተባባሪነት የምንሰራበት ነው

*የመልዕክቱ አይነት:- የጥፋት/የቅጣት መልዕክት የበረከት ወይም የተስፋ ቃል መልእክት ካለው ቅድመ ሁኔታ አለው*

- *የጥፋት/የቅጣት መልዕክት*
  - ✓ ይህ ስለ እርሱ የተናገርሁበት ሕዝብ ከክፋቱ ቢመለስ፥ እኔ አደርግበት ዘንድ ካሰብሁት ክፉ ነገር እጸጸታለሁ። (ኤር18፥8)

  ስለዚህ ስለ ሀገር ስለ ህዝብ ስለ ግለሰብ ሰለ ቤተሰብ መጥፎ ትንቢት ቢመጣ ስለ ጥፋት የመጣው የትንቢቱ መልዕክት መሠረት ያለው ከሆነ ንስሐ በቶሎ መግባት :: ስለ ሌሎች ከሆነ መማለድ እጅግ ያስፈልጋል::

  - ❖ ዮናስም ተነሥቶ እንደ እግዚአብሔር ቃል ወደ ነነዌ ሄደ፤ ነነዌም የሦስት ቀን መንገድ ያህል እጅግ ታላቅ ከተማ ነበረች። ...የነነዌም ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ፤ ለጾም

አዋጅ ነገሩ፥ ከታላቁም ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ ማቅ ለበሱ … እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ፤ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም። **(ዮናስ 3: 3,5,10)**

- ❖ እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ በትርህን ውሰድ፤ አንተና ወንድምህ አሮን ማኅበሩን ሰብስቡ፥ ድንጋዩም ውኃን እንዲሰጥ እነርሱ ሲያዩ ተናገሩት፤ ከድንጋዩም ውኃ ታወጣላቸዋለህ፤ እንዲሁም ማኅበሩን ከብቶቻቸውንም ታጠጣላቸዋለህ።ሙሴም እንደ ታዘዘ በትሩን ከእግዚአብሔር ፊት ወሰደ። ሙሴና አሮንም ጉባኤውን በድንጋዩ ፊት ሰብስበው፦ እናንተ ዓመፀኞች፥ እንግዲህ ስሙ፤ በውኑ ከዚህ ድንጋይ ውኃን እናወጣላችኋለን? አላቸው። ሙሴም እጁን ዘርግቶ ድንጋዩን ሁለት ጊዜ በበትሩ መታው፤ ብዙም ውኃ ወጣ፥ ማኅበሩም ከብቶቻቸውም ጠጡ።እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን፦ በእስራኤል ልጆች ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ በእኔ አላመናችሁምና ስለዚህ ወደ ሰጠኋቸው ምድር ይህን ጉባኤ ይዛችሁ አትገቡም አላቸው። (ዘኍ 20:10) (ወደ ተስፋይቱ ምድር ህዝቡን እንዲያስገባ የተነገረለት ሙሴ ራሱ አልገባም)

❖ **ስንት ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ በግል በቤተሰብ ደረጃ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ በሀገር ደረጃ ያስጠነቀቀን ነገር ደረሰብን (እንደ እንጉሡ ሰሎሞን) ሳንቀበላቸውና የሚገባን ሳናደርግ ቀርተን።**

- *የበረከት ወይም የተስፋ ቃል መልእክት ካለው ቅድመ ሁኔታ አለው*
  - የበረከት/የተስፋ ትንቢቶች በእምነት ካልተቀበሉዋቸው ወይም ቅድመ ሁኔታዎቹ ካልተሟሉ ሊቀሩ ይችላሉ።
    - ✓ ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በቀር በእርስዋ አስቀምጣችሁ ዘንድ እጄን ዘርግቼ ወደ ማልሁላችሁ ምድር በእውነት እናንተ አትገቡም። (ዘኍ 14: 30)
    - ✓ በፊቴ ክፉን ነገር ቢያደርግ ቃሌንም ባይሰማ፥ እኔ አደርግለት ዘንድ ስለ ተናገርሁት መልካም ነገር እጸጸታለሁ። (ኤር 18፥10)
    - ✓ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋልና። (ዕብ 10: 36)

ከእግዚአብሔር የትንቢት መልእክት ሲመጣ በሥር ዓት መዝግቦ መያዝና ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ መገኘት (የእኛን ድርሻ በመወጣት/የአፈጻጸሙን ሂደት በመከታተል) ያስፈልጋል::

- ✓ በጸሎት የተስፋ ቃሉን በማሳሰብ/በመጠየቅ
  "እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፦ ሰባው ዓመት በባቢሎን በተፈጸመ ጊዜ እጐበኛችኋለሁ፥ ወደዚህም ስፍራ እመልሳችሁ ዘንድ መልካሚቱን ቃሌን እፈጽምላችኋለሁ።" (ኤር 29: 10)
  "በነገሡ በመጀመሪያው ዓመት እኔ ዳንኤል የኢየሩሳሌም መፍረስ የሚፈጸምበትን ሰባውን ዓመት፥ እግዚአብሔር በቃሉ ለነቢዩ ለኤርምያስ የተናገረውን የዓመቱን ቍጥር በመጽሐፍ አስተዋልሁ። ማቅ ለብሼ በአመድም ላይ ሆኜ ስጾም እጸልይና እለምን ዘንድ ፊቴን ወደ ጌታ ወደ አምላክ አቀናሁ። (ዳን 1:2-3)

**ስንት ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ በግል በቤተሰብ ደረጃ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ በሀገር ደረጃ የተናገረን የተስፋ ቃሎች ሳይፈጸሙ ቀሩ ሳንቀበላቸውና የሚገባን ሳናደርግ ቀርተን።**

*ሐ) የተፈጻሚነት ሽፋን*

1. ለአንድ ሰው/ አካል ብቻ የሚሠራ
   - ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፥ የልዑል ነቢይ ትባላለህ፥ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና፤ (ሉቃ 1: 76)
   - ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል፥ በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል አላት።(ሉቃ 2:35)

2. ከአንድ ሰው/አካል የሚያልፍ በተቀበሉት ሁሉ የሚሰራ
   - ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጐበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤ (ኢዮ 2:28)
   - በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ። (2ዜና 7፥14)

3. በሀገር ደረጃ የሚመጣ ትንቢት
   - ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።
4. በምድር ሁሉ የሚሆን ትንቢት
   - የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፦ ገና አንድ ጊዜ በቅርብ ዘመን እኔ ሰማያትንና ምድርን ባሕርንና የብስንም አናውጣለሁ፤ (ሐጌ 2፥6)

❖ **በእያንዳንዱ የትንቢት አይነት እንደ ትንቢቱ ባህርይ ልንጠብቅ እና የሚገባንን ልናደርግ ይገባል።**

*መ) የመልዕክቱ ግልጽነት ደረጃ*
*ትንቢት ሁሉ ፍጹም አይደለም*

❖ ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤ (1ቆሮ 13፥9)
❖ ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል። ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤ ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል። (1ቆሮ 13:8-10)

✓ አያሌ ቀንም ተቀምጠን ሳለን ነቢይ የነበረ አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ከይሁዳ ወረደ። ወደ እኛም መጣና የጳውሎስን መታጠቂያ ወስዶ የገዛ እጁንና እግሩን አስሮ፦ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ፦ ይህ መታጠቂያ ያለውን ሰው ***አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደዚህ ያስሩታል በአሕዛብም እጅ አሳልፈው ይሰጡታል*** ይላል አለ። ይህንም በሰማን ጊዜ እኛም በዚያ የሚኖሩትም ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ ለመንነው። ጳውሎስ ግን መልሶ፦ እያለቀሳችሁ ልቤንም እየሰበራችሁ ምን ማድረጋችሁ ነው? እኔ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳ ተሰናድቼአለሁ እንጂ ለእስራት ብቻ አይደለም አለ። ምክርንም ሊቀበል እምቢ ባለ ጊዜ፦ የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን። (ሐዋ 21: 10-14)

✓ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤(ሮሜ 12፥6)
   - የትንቢት መልእክት አስተላላፊው እምነት እና የመንፈሳዊ መረዳት ደረጃ ላይ ሊደገፍ ይችላል።

**ማሳሰቢያ**

- ወዳጆች ሆይ፥ ***መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥*** ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና። (1ዮሐ 4፥1)
- ***መንፈስን አታጥፉ***፤ትንቢትን አትናቁ፤ ***ሁሉን ፈትኑ*** መልካሙንም ያዙ፤ (1ተሰ5፥19-21)
   - ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተባለው ነው። እግዚአብሔር ይላል፦ በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤ ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ። (ሐዋ 2:16-18)
   ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጐበዞቻችሁም

ራእይ ያያሉ፤ (ኢዮ 2: 28) (ይህ በቤተ ክርስቲያን እንግዳ ነገር ሳይሆን የተለመደ ክስተት መሆን ነው የሚገባው- this needs to be common in the Church)

ትንቢትን እና ነቢያትን ሁሉ ከሚቃወም እና ተጠንቀቁ በሌላ በኩል ደግሞ ትንቢትን ሁሉ እና ነቢያት የተናገሩትን ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንውሰድ የሚልም የተሳሳተ ነው።

- መጽሐፍ ቅዱሳዊው ሚዛናዊዉን እንፈልግ (መንፈስን አናጥፋ ትንቢትን አንናቅ የሚለ እና ሁሉን እንፈትን መልካሙን እንያዝ እንጠንቀቅ የሚል ነው። ትንቢት ስጦታን እንፈልግ...... ከሐሰት ትንቢት እና ከሀሰተኛ ነቢያት እንጠንቀቅ..... ሁለቱን መጸሐፍ ቅዱሳዊ እና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንያዝ።

# ክፍል ሦስት:
# አመራር እና አደረጃጀት

## I. መንፈሳዊ ስጦታዎች የተሰጡት ለቤተ ክርስቲያን ነው። በአገባብና በሥርዓት አስረዳዳሪዋም ቤተክርቲያን ናት

- እግዚአብሔርም **በቤተ ክርስቲያን** አንዳንዶቹን:- አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ... አድርጎአል። (1ኛ ቆሮ 12፥28)
- እንዲሁ ደግሞ እናንተ መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ። (1ቆሮ 14፥12)
- ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው፤ .... እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና፤ በቅዱሳንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲህ ነው። (1 ቆሮ 14: 29,33)
- የጸጋ አገግሎት ጥሪ ያለው ሐዋርያ ቢሆን ነቢይ ወይ ወንጌል ሰባኪ... ወይም ሌላ የተጡት ለቤተ ክርስቲያን ነው እንጂ ቤተ ክርስቲያን በእነርሱ ሥር እንድትሆን አልተሰጠችም። ሆኖም ግን በቤተ ክርስቲያን አመራር በኩል ያለ ክፍተት አብሮ መሥራት እስከማይቻል ድረስ የደህንነት እና የመሠረተ እምነት ጉዳይ ሆኖ በክርስቶስ አካል ውስጥ ሊኖር የሚገባን የመንፈስ አንድነት የሚያጠፋ ሊሆን አይገባም ።
- መጽሐፍቅ ዱሳዊውን እና የተሻለውን የቤተ ክርስቲያን አመራር እና አስተዳደር የምታሳይ ምሳሌ /ሞዴል ቤተ ክርስቲያን መገለጥ አለባት። ያለበለዚያ መነቃቀፍ ብቻ ነው የሚሆነው (በሽማግሌዎች አስተዳደር የምትመራው በአንድ አገልጋይ የምትመራውን ስትነቅፍ ያኛው ይህንን ሲነቅፍ መኖር እና ለክርስቶስ አካል መዳከም አስተቃጾ ማድረግ ነው የሚሆነው። የተሻለውን የቤተክርስቲያን መጽሐፍቅዱሳዊ አመራር በትምህርት ብቻ ሳይሆን በተግባርም ማሳየት ያስፈልጋል። ለዚህም እንሰራለን።

## II. በቤተ ክርስቲያን የጸጋ ሥጦታን እና 5ቱን የጸጋ የአገልግሎት ጥሪዎችን በሙላት መገለጥ በሚመለከት ሊኖር የሚገባ አመራር እና አደረጃጀትምን አይነት ነው? (የትንቢተና የነቢያት አገግሎትን በሚመለከት)

- በዓለም ላይ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የቤተ ክርስቲያን አመራርን በሚመለከት ትልቅ ተግዳሮት አለ። ተጠሪነት እና ተጠያቂነት የሌለው የቤተ ክርስቲያን አመራር ነው። ጥፋቶቹም ጉዳቶቹም ብዙ ናቸው።
- የእንደዚህ አይነት አመራር ዋና ችግሮች የክርስቶስ ኢየሱስ ራስነት ይሸፈናል። ዋና አገልጋዩ ይጎላል። ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ የአገልግሎት ጥሪዎችም ሆኑ የጸጋ አገልግሎቶች በሙላት መገለጥ አይችሉም። ከ5ቱ የጸጋ አገልግሎት ጥሪዎች አንዱ የተሰጡት ቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን በጣ ም የተለመደ ነው። ብዙ ክፍቶች እና ችግሮች ያሉት ነው።
- በአንጻሩ ደግሞ የአገልግሎት ጥሪዎች በቤተክርስቲያን ሥር በሙላት እንዲገለጡ ወይንም ሲገለጡ በቤተ ክርስቲያን ሊኖራቸው የሚገባ ስፍራ: ኃላፊነት እና የአሠራር ነጻነት ምንድነው? አንድ መሠረታዊ ሊታወቅ የሚገባ ነገር 5ቱም የአገልግሎት ጥሪዎች በየጥሪያቸው አቅጣጫ የቤተክርስቲያን አመራር አስተዋጾ ያላቸው መሆኑ ነው። አስተማሪ መንፈሳዊ እውነት እና መንፈሳው እድገት ከማምጣት አኳያ በትምህርቱ ይመራል። ነቢዩ በትንቢታዊ መልዕክቱ ቤተ ክርስቲያን የምትሔድበትን አቅጣጫ ያሳያል ወዘተ... ሌሎችም እንደየጥሪያቸው። የሽማግሌዎች አስተዳደር ሁሉም በስፍራቸው እንዲገለጡ እና ቤተ ክርስቲያን በአንድ አካልነት ወደ ሙላት እንድታድግ ሁሉን የማስተባበር እና የመምራት ሚና ይጫወታሉ።